የኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ ባለሥልጣን

ETHIOPIAN CAPITAL MARKET AUTHORITY

# መመሪያ ቁጥር 1031/2017

# ራሳቸውን በራሳቸው የሚቆጣጠሩ ድርጅቶች እውቅና አሰጣጥ እና ቁጥጥር መመሪያ

ማውጫ

ክፍል አንድ፡ ........ 5
ጠቅላላ ድንጋጌዎች ........ 5
1. አጭር ርዕስ........ 5
2. ትርጓሜዎች ........ 5
3. የተፈጻሚነት ወሰን........ 6
ክፍል ሁለት........ 6
እውቅና ለማግኘት የሚቀርብ ማመልከቻ ........ 6
4. ክልከላ........ 6
5. የማመልከቻ አቀራረብ ........ 6
6. የተለዩ የእውቅና መስፈርቶች ........ 7
7. ክፍያዎች ........ 8
8. የእውቅና ማመልከቻ ተቀባይነት ........ 8
9. እውቅና ለማግኘት የሚቀርብ ማመልከቻን ውድቅ ስለማድረግ ........ 9
10. ማመልከቻ ስለሚስተናገድበት ጊዜ ........ 9
ክፍል ሦስት ........ 10
ጠቅላላ ግዴታዎችና ኃላፊነቶች........ 10
11. ራሳቸውን በራሳቸው የሚቆጣጠሩ ድርጅቶች ገለልተኛነት እና አስተዳደር ........ 10
12. ራሳቸውን በራሳቸው የሚቆጣጠሩ ድርጅቶች ግዴታዎች........ 10
13. ራሱን በራሱ ለሚቆጣጠር ድርጅት ስልጣንና ሀላፊነቶች ........ 10
14. ራሱን በራሱ የሚቆጣጠር ድርጅት የገንዘብ ሀብቶች እና አስተዳደራዊ አቅም ........ 11
15. ራሱን በራሱ የሚቆጣጠር ድርጅት የሰው ኃይል........ 11
16. ራሱን በራሱ የሚቆጣጠር ድርጅት የአስተዳደር መዋቅር ........ 12
17. ራሳቸውን በራሳቸው የሚቆጣጠሩ ድርጅቶች እና ሰራተኞቻቸው የብቁና የተገቢነት መስፈርቶች........ 12
18. ዋና የሕግ ማስከበር መኮንን ........ 13
19. ጉልህ ለውጦች........ 13
20. ራሱን በራሱ የሚቆጣጠር ድርጅት ቢሮ ........ 14
21. ሪከርዶችን ስለመጠበቅ ........ 15
22. ሪፖርት የማድረግ ግዴታ ........ 15



የኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ ባለስልጣን
ETHIOPIAN CAPITAL MARKET AUTHORITY

23. ስርዓቶች እና ቁጥጥሮች ........ 16

24. በባለስልጣኑ የሚደረግ ክትትል እና ምርመራ ........ 16

25. ከምርመራ ወይም ከክትትል ጋር በተያያዘ የሚደረግ ትብብር ........ 17

26. የደንበኞች ካሣ ፈንድ ........ 17

ክፍል አራት ........ 17

አስተዳደራዊ እርምጃዎች ........ 17

27. ቅጣቶች እና ሌሎች ........ 17

28. እውቅናን ማንሳት ........ 18

29. ይግባኝ የመጠየቅ ስነ-ስርዓት ........ 19

ክፍል አምስት ........ 19

ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች ........ 19

30. ተፈጻሚነት የማይኖራቸው መመርያዎች ........ 19

31. መመሪያው የሚጸናበት ቀን ........ 19

ራሳቸውን በራሳቸው የሚቆጣጠሩ ድርጅቶች ለገበያ ተሳታፊዎች የስነምግባር ደረጃዎችን በማዘጋጀት እና በማስፈጸም፣ ፍትሃዊ ውድድርን በማጎልበት እና የባለስልጣኑን የቁጥጥር ሀላፊነት ጫና በመቀነስ ረገድ ጠቃሚ ሚና የሚጫወቱ በመሆኑ፣

የኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ ባለስልጣን ከኃላፊነቶቹ ውስጥ እንዳስፈላጊነቱ የተወሰኑትን ስልጣን እና ሀላፊነትን በውክልና እውቅና ለሚሰጠው ራሱን በራሱ ለሚቆጣጠር ድርጅት የሚያስተላልፍበትን ስርዐት በመመሪያ እንዲወስን በካፒታል ገበያ አዋጁ ስልጣን የሰጠው በመሆኑ፣

ባለስልጣኑ በካፒታል ገበያ አዋጁ ክፍል ሶስት እና አንቀጽ 108(2) መሠረት ይህን ራሳቸውን በራሳቸው የሚቆጣጠሩ ድርጅቶች እውቅና አሰጣጥ መመሪያ አውጥቷል።

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "ራሳቸውን በራሳቸው የሚቆጣጠሩ ድርጅቶች እውቅና አሰጣጥ እና ቁጥጥር መመሪያ ቁጥር 1031/2017" ተብሎ ይጠራል፡፡

2. ትርጓሜዎች

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

1) ‹‹ባለስልጣን›› ማለት በአዋጁ የተቋቋመው የኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ ባለስልጣን ነው።
2) ‹‹ዋና የሕግ ማስከበር መኮንን›› ማለት ራሱን በራሱ የሚቆጣጠር ድርጅት አዋጁን፣ ይህን መመሪያ፣ የውስጥ ደንቦች እና የአሰራር ስርዐቶቹን እንዲሁም ሌሎች አግባብነት ያላቸው ሕጎችን አክብሮ እንደሚሰራ የማረጋገጥና የመከታተል ኃላፊነት የተሰጠው ሰራተኛ ነው፡፡
3) ‹‹የሒሳብ ዓመት›› ማለት እ.ኤ.አ ከሐምሌ አንድ ጀምሮ የሚቆጠር የአስራ ሁለት ወራት ጊዜ ነው፡፡
4) ‹‹ገለልተኛ ዳይሬክተር›› ማለት በዚህ መመሪያ የተቀመጠውን የገለልተኛ ሰው ትርጓሜ የሚያሟላ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባል ነው፡፡
5) ‹‹ገለልተኛ ሰው›› ማለት ራሱን በራሱ ከሚቆጣጠር ድርጅት ጋር ወይም ራሱን በራሱ ከሚቆጣጠር ድርጅት ጋር ግንኙነት ካለው ሌላ ድርጅት ጋር ፤ ወይም ራሱን በራሱ የሚቆጣጠር ድርጅት ውስጥ አባል ከሆነ ድርጅት ጋር ወይም ከአባሉ ጋር ቅርበት ካለው ሌላ ድርጅት ጋር ወይም ራሱን በራሱ በሚቆጣጠር ድርጅት ገበያ ወይም አገልግሎት ላይ ከተመዘገቡ፣ ግብይት ከሚደረግባቸው ወይም ክፍያ ከሚፈጸምባቸው ሰነደ ሙዓለንዋዮች አውጪ ጋር ጉልህ ግንኙነት የሌለው ግለሰብ ነው፡፡
6) ‹‹ጉልህ ግንኙነት›› ማለት በክፍያ፣ ወይም በቤተሰባዊ ግንኙነት ወይም በሌላ ማናቸውም ግንኙነት ላይ የተመሰረተና የገለልተኛው ሰው ውሳኔ ላይ ወይም ውሳኔ አሰጣጥ ላይ ተጽዕኖ ሊያሳድር የሚችል ግንኙነት ነው፡፡
7) ‹‹ሰው›› ማለት ማንኛውም የተፈጥሮ ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው ሰው ነው፡፡
8) ‹‹አዋጅ›› ማለት የካፒታል ገበያ አዋጅ ቁጥር 1248/2013 ነው።
9) በዚህ መመሪያ ውስጥ በወንድ ፆታ የተገለጸው ሴትንም ያካትታል፡፡
10) በዚህ መመሪያ የተገለጸ ማናቸውም ቃል በአዋጁ የተሰጠው ትርጉም ይኖረዋል።

3. የተፈጻሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ በሚከተሉት ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

(1) ባለስልጣኑ የሚቆጣጠረው ተቋም ሆኖ በአዋጁና በዚህ መመሪያ መሰረት ራሱን በራሱ የሚቆጣጠር ድርጅት ሆኖ እውቅና በተሰጠው ተቋም፣

(2) ከቁጥጥር ስራቸው ጋር በተገናኘ በየሰነደ ሙዓለንዋዮችይ ገበያ እና የሰነደ ሙዓለንዋዮች አጣሪና ክፍያ ፈጻሚ ኩባንያ፣

## ክፍል ሁለት

## እውቅና ለማግኘት የሚቀርብ ማመልከቻ

4. ክልከላ

በአዋጁ አንቀፅ 22(2) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ይህን እንዲሰራ በባለስልጣኑ ዕውቅና ከተሰጠው ተቋም በስተቀር ማንኛውም ተቋም በኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ ውስጥ ራሱን በራሱ የሚቆጣጠር ተቋም ሆኖ መስራት አይችልም።

5. የማመልከቻ አቀራረብ

(1) እውቅና ለማግኘት የሚቀርብ ማመልከቻ ባለስልጣኑ አዋጁን እና ይህን መመሪያ መሰረት አድርጎ በሚያዘጋጃቸው ቅጾችና የአሰራር ስርዐቶች መሰረት መቅረብ ይኖርበታል።

(2) ሁሉም ማመልከቻዎችና አባሪ ሰነዶች ለባለስልጣኑ መቅረብ ያለባቸው በእንግሊዝኛ ወይም በአማርኛ ቋንቋ መሆን አለበት፡፡ ማንኛውም መረጃ ወይም ሰነድ በሌላ ማንኛውም ቋንቋ የቀረበ ከሆነ ከተረጋገጠ የእንግሊዝኛ ወይም የአማርኛ ትርጉም ጋር ተያይዞ መቅረብ አለበት፡፡

(3) የማመልከቻ ክፍያ የተፈጸመና የምዝገባ መስፈርቶች የተሟሉ ቢሆንም አመልካቹ ለስልሳ (60) የካላንደር ቀናት ለባለስልጣኑ በአግባቡ ሳያሳውቅና ሳይፈቀድለት የማመልከቻ ሂደቱን ሳይከታተል የቀረ እንደሆነ ባለስልጣኑ እውቅና ለማግኘት የተጀመረውን ሂደት ሊያቋርጥ ይችላል፡፡

6. የተለዩ የእውቅና መስፈርቶች

(1) በአዋጁ አንቀጽ 22(4) ከተደነገጉት መስፈርቶች በተጨማሪ እውቅና ለማግኘት የሚቀርብ ማመልከቻ የሚከተሉትን ማካተት ይኖርበታል፡-

ሀ) በባለስልጣኑ የተወሰነውን ክፍያ መከፈሉን የሚያረጋግጥ ማስረጃ፤

ለ) አግባብ ባለው የመንግስት አካል የተሰጠ የምስረታ ሰነድ ፤

ሐ) ማመልከቻው በቀረበበት ጊዜ ያሉትን የአመልካቹን ዳይሬክተሮች፣ አባላቱንና ካፒታሉን የሚያሳዩ አግባብነት ያላቸው የምስረታ ሰነዶች፤

መ) ድርጅቱ እውቅና ሲያገኝ ማከናወን የሚፈልጋቸው ተግባራትና ሀላፊነቶች ዝርዝር ፤

ሠ) ከኢትዮጵያ ሕግ እና በየወቅቱ በስራ ላይ ከሚውሉ ዓለም-አቀፍ መስፈርቶች ጋር የተጣጣሙ በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ ወይም ንብረት ሕጋዊ አስመስሎ ማቅረብን እና ሽብርተኝነትን በገንዘብ መርዳትን ለመከላከል የተዘጋጁ አሰራሮችን ጨምሮ፣ ራሱን በራሱ የሚቆጣጠረው ድርጅት አባላት የሚገዙባቸው በስራ ላይ ያሉ ወይም ምክረ-ሃሳብ የቀረበባቸው ደንቦች፣ ፖሊሲዎች፣ እና ሌሎች መሰል ሰነዶች፤

ረ) የአመልካቹ ድርጅታዊ መገለጫ፤

ሰ) የአመልካቹን የኃላፊነት ተዋረድ በግልጽ የሚያሳይ ድርጅታዊ መዋቅር፤

ሸ) ማመልከቻው በቀረበበት ዕለት በአመልካቹና በከፍተኛ ባለሙያዎቹ የተፈረመ አባላቱ ለካፒታል ገበያ አገልግሎት ሰጪዎች፣ ለሰራተኞቻቸውና ከፍተኛ ተጽዕኖ ላላቸው ሰዎች የወጣውን የስነ ምግባር ደንብ እና የካፒታል ገበያ አዋጅና አዋጁን ተከትለው የወጡ ሌሎች ህጎችን እንደሚያከብሩ ቃል የገቡበት ስምምነት ፤

ቀ) ማመልከቻው በቀረበበት ዕለት አመልካቹ አስራ ሁለት (12) ወራት ወይም ከዚያ ጊዜ በላይ በስራ ላይ የቆየ ከሆነ ማመልከቻው ከቀረበበት ቀን በፊት ላለቀው የሂሳብ ዓመት በኦዲተር የተረጋገጠ የሂሳብ መግለጫ እና ለተቀሩት ወራት በኦዲተር ያልተረጋጋጠ የሂሳብ መግለጫ፤

በ) አመልካቹ ከአስራ ሁለት (12) ወራት ላነሰ ጊዜ በስራ ላይ የቆየ ከሆነና ነገር ግን የፋይናንስ ዓመቱ ካለቀ፣ ይህንኑ ጊዜ የሚሸፍን የተመረመረ የሂሳብ መግለጫ፣

ተ) አመልካቹ ከአስራ ሁለት (12) ወራት ላነሰ ጊዜ በስራ ላይ የቆየ ከሆነና ነገር ግን የፋይናንስ ዓመቱ ካላለቀ፣ ይህንኑ ጊዜ የሚሸፍን በኦዲተር ያልተረጋገጠ የሂሳብ መግለጫ፤ይሁን እንጂ አመልካቹ የፋይናንስ ዓመቱ ካለቀ በኋላ በሦስት ወራት ውስጥ በኦዲተር የተረጋገጠውን የሂሳብ መግለጫ ለባለስልጣኑ ማቅረብ አለበት፤

ቸ) በባለስልጣኑ በዚህ መመሪያ ባስቀመጠው መሰረት ለያዙት ሚና እና ሀላፊነት የተቀመጡ የብቁና እና ተገቢነት መስፈርቶችን የሚያሟሉ ከፍተኛ ባለሙያዎችን ዝርዝር መረጃ፤

ኀ) በዚህ መመሪያ አንቀጽ 17 በሚጠየቀው መሰረት ከወንጀል ነጻ መሆኑን የሚያስረዳ የምስክር ወረቀት፤

ነ) ራሱን በራሱ እንደሚቆጣጠር ድርጅት የሚያስፈልገው የፋይናንስ ሀብትና አስተዳደራዊ አቅም ያለው መሆኑን የሚያረጋግጥ ማስረጃ፣

ኘ) ራሱን በራሱ እንደሚቆጣጠር ድርጅት የሚያስፈልገው የቴክኖሎጂ አቅም፣ የውስጥ ቁጥጥር፣ እና የስጋት አስተዳደር ስርዓት ያለው መሆኑን የሚያረጋግጥ ማስረጃ፤

አ) የአመልካቹ የተመዘገበ ቢሮ አድራሻ እና የታሰበ ዋና መስሪያ ቤት አድራሻ (ከተመዘገበው የቢሮ አድራሻው የተለየ ከሆነ) እና ሌላ ማንኛውም አመልካቹ ስራውን ለማከናወን ያሰበበት ቢሮ አድራሻ፤ እና

ከ) በአዋጁ ወይም በዚህ መመሪያ በተቀመጠው አግባብ ራሱን በራሱ ከሚቆጣጠር ድርጅት ሀላፊነት ጋር በተገናኘ ሌላ ማንኛውም ባለስልጣኑ የሚጠይቀው መረጃ

(2) ሁሉም በማመልከቻ ቅጽ ላይ ያሉ ጥያቄዎች እውነተኛና ትክክለኛ መልስ ሊሰጣቸው ይገባል፡፡

(3) በማመልከቻ ሂደቱ ወቅት ዋና የሕግ ማስከበር መኮንኑን ጨምሮ ቢያንስ ሦስት (3) የአመልካቹ ከፍተኛ አመራሮች በባለስልጣኑ ተወካዮች ቃለ መጠይቅ ሊደረግላቸው ይገባል፡፡

(4) አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ራሱን በራሱ የሚቆጣጠረው ድርጅት ሌሎች ከፍተኛ ባለሙያዎች በባለስልጣኑ ተወካዮች ቃለ መጠይቅ ሊደረግላቸው ይችላል፡፡

(5) እውቅና ለማግኘት የሚደረግ ማመልከቻ እንደቀረበ የሚቆጠረው ሁሉም አስፈላጊ ሰነዶች ለባለስልጣኑ ተሟልተው ሲቀርቡ ነው፡፡

7. ክፍያዎች

(1) እያንዳንዱ የእውቅና አመልካች በባለስልጣኑ የክፍያ መመሪያ የሚወሰነውን የማይመለስ የማመልከቻ እና የዕውቅና ክፍያ መክፈል አለበት።

8. የእውቅና ማመልከቻ ተቀባይነት

በዚህ መመሪያ አንቀጽ 6 እና 7 የተቀመጡት መስፈርቶች ሲሟሉ ባለስልጣኑ፡-

(1) አመልካቹ እውቅና የተሰጠው ራሱን በራሱ የሚቆጣጠር ድርጅት መሆኑን የሚገልጽ ውሳኔውን ለአመልካቹ በጽሁፍ ያሳውቀዋል፤

(2) ድርጅቱ ራሱን በራስ የሚቆጣጠር ድርጅት ሆኖ ዕውቅና የተሰጠው መሆኑን በኢትዮጵያ ውስጥ ሰፊ ስርጭት ባለው ጋዜጣ ለህዝቡ ያሳውቃል፡፡

9. እውቅና ለማግኘት የሚቀርብ ማመልከቻን ውድቅ ስለማድረግ

(1) አመልካቹ፡-

ሀ) ከአዋጁ፣ ወይም አዋጁን ተከትለው ከወጡ ህጎች ጋር የማይጣጣሙ ውስጠ-ደንቦችና ፖሊሲዎች ያሉት፤

ለ) ስራውን ለማከናወን በቂ አቅምና ብቃት ያላቸው ሰራተኞች ያሉት መሆኑን ማሳየት ያልቻለ፣

ሐ) ሀሰተኛ ወይም አሳሳች መረጃ የሰጠ፣

መ) እውቅና ለማግኘት ማመልከቻ ባቀረበበት ወቅት ጉልህ መረጃን ያስቀረ ወይም ለባለስልጣኑ መቅረብ የነበረበትን ማንኛውንም መረጃ ሳይገልጽ የቀረ፤

ሠ) እውቅና ለማግኘት ባለስልጣኑ ከአዋጁ ጋር በተጣጣመ መንገድ ባወጣቸው መመሪያዎች እና በሌሎች የባለስልጣኑ ሰነዶች የተገለጹ የብቁና ተገቢነት፣ የፋይናንስ ሀብትና አስተዳደራዊ አቅም፣ የውስጥ አደረጃጀትና የስጋት አስተዳደር፣ እና ሌሎች የቁጥጥርና የክትትል መስፈርቶችን ያላሟላ፤ ወይም

ረ) ማንኛውንም የአዋጁን፣ የዚህን መመሪያ ወይም ሌሎች አግባብነት ያላቸውን ሕጎች ድንጋጌዎች የጣሰ

መሆኑ ከተረጋገጠ ባለስልጣኑ እውቅና ለማግኘት የቀረበውን ማመልከቻ ውድቅ ሊያደርገው ይችላል፡፡

(2) ማንኛውም አመልካች ራሱን በራስ የሚቆጣጠር ድርጅት ለመሆን ያቀረበው ማመልከቻ ውድቅ የማድረግ ውሳኔ ከመሰጠቱ በፊት በባለስልጣኑ የመሰማት እድል ሊሰጠው ይገባል፡፡

10. ማመልከቻ ስለሚስተናገድበት ጊዜ

(1) በዚህ መመሪያ አንቀጽ 6 መሰረት የተሟላ ማመልከቻ በቀረበ በአስራ አምስት (15) ቀናት ውስጥ ባለስልጣኑ ለአመልካቹ ውሳኔውን በጽሁፍ ማሳወቅ አለበት፡፡

(2) ውሳኔው አመልካቹን ራሱን በራስ የሚቆጣጠር ድርጅት እንዲሆን እውቅና መስጠት ከሆነ ባለስልጣኑ አመልካቹ ተገቢውን የእውቅና ክፍያ እንዲከፍል ያደርጋል፡፡

## ክፍል ሦስት

## ጠቅላላ ግዴታዎችና ኃላፊነቶች

11. ራሳቸውን በራሳቸው የሚቆጣጠሩ ድርጅቶች ገለልተኛነት እና አስተዳደር

(1) ራሳቸውን በራሳቸው የሚቆጣጠሩ ድርጅቶች እንደአግባብነቱ የቁጥጥር ተግባራቸውንና የንግድ ተግባራቸውን ለያይተው መምራት የሚያስችላቸው ፖሊሲ እና አሰራር መተግበርና ለሁለቱም ተግባራት የተለያየ የሰው ኃይል መመደብ አለባቸው፡፡

(2) ከቁጥጥር ስራ ጋር በተያያዘ የሚሰበሰብ መቀጮና የአገልግሎት ክፍያ ለቁጥጥር አገልግሎት ብቻ መዋል አለበት፤ እንዲሁም እያንዳንዱ ራሱን በራሱ የሚቆጣጠር ድርጅት ከመቀጮ እና ከአገልግሎት ክፍያ የሚሰበሰብ ገንዘብን የሚጠቀምበት ፖሊሲ በአዋጁ አንቀጽ 24(1) መሰረት በሚያወጣው ውስጠ ደንቡ ላይ ሊያስቀምጥ ይገባል፡፡

(3) ራሳቸውን በራሳቸው የሚቆጣጠሩ ድርጅቶች በአዋጁ ፣ በዚህ መመሪያ እና በሌሎች አግባብነት ባላቸው ሕጎች የተቀመጡ የባለቤትነት ገደቦችንና የመልካም አስተዳደር መስፈርቶች መከበራቸውን ማረጋገጥ አለባቸው፡፡

12. ራሳቸውን በራሳቸው የሚቆጣጠሩ ድርጅቶች ግዴታዎች

ራሱን በራሱ የሚቆጣጠር ድርጅት የሚከተሉትን ማድረግ አለበት፡-

(1) ፈቃድ ያላቸውን የካፒታል ገበያ አገልግሎት ሰጪዎች ብቻ በአባልነት መቀበል፤
(2) ፍትሃዊና ግልጽነት ያለው አባላትን የሚቀበልበትን አሰራር መዘርጋት፤
(3) በስራዎቹ ለኢንቨስተር ጥበቃ ቅድሚያ መስጠት፤
(4) ለገበያ ተዐማኒነት መስራት፤
(5) መዋቅራዊ ስጋትን ለመቀነስ መስራት፤ እና
(6) የስልጠና እና የአቅም ግንባታ ተግባራትን ማከናወንን ጨምሮ የካፒታል ገበያን ስነ-ምህዳር ለማሳደግ መስራት።

13. ራሱን በራሱ ለሚቆጣጠር ድርጅት ስልጣንና ሀላፊነቶች

(2) በባለስልጣኑ መጽደቁ እንደተጠበቀ ሆኖ ራሱን በራሱ የሚቆጣጠር ድርጀት እንደአግባብነቱ የአባላቱ እና የሰነደሙዓለንዋይ አውጭዎች ስነምግባርና የስራ እንቅስቃሴ የሚመራበትን የውስጥ ደንብና መመሪያዎችን የማዘጋጀትና የማውጣት ስልጣን ይኖረዋል።

(3). ራሱን በራሱ የሚቆጣጠር ድርጅት የሚከተሉትን ተግባራት የማከናወን ስልጣን ይኖረዋል፡-

ሀ) ለአባላቱ ዝቅተኛ የስራ እንቅስቃሴመስፈርቶችን የማውጣት፤

ለ) ውስጠ ደንቦቹን የማስከበር እና በውስጠ ደንቦቹ መሰረት በአባላቱ ላይ የዲሲፕሊን እርምጃ መውሰድ ፤

ሐ) በአባላቱ ላይ በስራ ቦታቸው በመገኘት ወይም በስራ ቦታቸው ላይ መገኘት ሳይስፈልገው መደበኛ ክትትል እንዲሁም ልዩ ምርምራ ማድረግ፣

መ) የአባላቱን የሂሳብ እና ከሂሳብ ውጭ ያሉ መዛግብትን መመርመር፤

ሠ) የገበያ ቅኝትና ምርመራዎችን ማከናወን፤

ረ) በአባላቱ መካከል እንዲሁም በአባልና በኢንቨስተር መካከል የሚኖሩ አለመግባባቶች የሚፈታበትን ስርዓት ማዘጋጀት፤ እና

ሰ) ሌላ ማንኛውም በባለስልጣኑ በውክልና የሚሰጥ ሀላፊነት፡፡

14. ራሱን በራሱ የሚቆጣጠር ድርጅት የገንዘብ ሀብቶች እና አስተዳደራዊ አቅም

(1) አንድ ተቋም ራሱን በራሱ የሚቆጣጠር ድርጅት ተብሎ እውቅና የሚያገኘው ተቋሙ ኃላፊነቶቹን ለመወጣት የሚያስችል የገንዘብ ሀብቶች እና አስተዳደራዊ አቅም ያለው መሆኑን ለባለስልጣኑ ሲያረጋግጥ ብቻ ነው፡፡

(2) አመልካቹ ኃላፊነቶቹን በአግባቡ ለማከናወን የገንዘብ ሀብቶች እና አስተዳደራዊ አቅምያለው መሆኑን ለመወሰን ባለስልጣኑ የሚከተሉትን ጉዳዮች ማገናዘብ አለበት፡-

ሀ) ራሱን በራሱ የሚቆጣጠረው ድርጅት ተጋላጭ የሆነባቸውን የአሰራርና ሌሎች ስጋቶች፤

ለ) ራሱን በራሱ የሚቆጣጠረውን ድርጅት ካፒታል መጠንና አወቃቀር፤

ሐ) እንደአግባብነቱ ራሱን በራሱ የሚቆጣጠረውን ድርጅት የመድን ፖሊሲዎች እና ዋስትናዎችን ጨምሮ ሌሎች የፋይናንስ ሀብቶች መጠንና አወቃቀር፣ እና

መ) የአመልካቹን ውስጠ-ደንቦችና አሰራሮች፡፡

15. ራሱን በራሱ የሚቆጣጠር ድርጅት የሰው ኃይል

(1) ራሱን በራሱ የሚቆጣጠር ድርጅት የድርጅቱን ስራ አመራርና አስተዳደር በበላይነት እንዲቆጣጠሩ የሚመድባቸው ሰዎች ለስራው በቂ ክህሎትና ልምድ ያላቸው መሆኑን ማረጋገጥ አለበት።

(2) እያንዳንዱ ራሱን በራሱ የሚቆጣጠረው ድርጅት ከፍተኛ ባለሙያዎችን ሲሾም የካፒታል ገበያ አገልግሎት ሰጪዎችን የብቃት ማዕቀፍ መስፈርቶችን መሟላትን ማረጋገጥ አለበት፡፡

16. ራሱን በራሱ የሚቆጣጠር ድርጅት የአስተዳደር መዋቅር

(1) ራሱን በራሱ የሚቆጣጠር ድርጅት የዳይሬክተሮች ቦርድ ገለልተኛ ዳይሬክተሮችንና የዘርፉ ባለሙያዎችን ያካተተ መሆን አለበት፡፡

(2) የገለልተኛ ዳይሬክተሮች ቁጥር የቦርዱን ቢያንስ አንድ-ሦስተኛ (1/3ኛ) መሆን አለበት፡፡

17. ራሳቸውን በራሳቸው የሚቆጣጠሩ ድርጅቶች እና ሰራተኞቻቸው የብቁና የተገቢነት መስፈርቶች

(1) ራሱን በራሱ የሚቆጣጠር ድርጅት እና ሰራተኞቹ ብቁና ተገቢ መሆናቸውን ለመወሰን ባለስልጣኑ በአዋጁ አንቀጽ 56 ላይ የተቀመጡ የብቁና ተገቢነት መስፈርቶችን ማሟላታቸውን ከግምት ያስገባል።

(2) ሁሉም ራሳቸውን በራሳቸው የሚቆጣጠሩ ድርጅቶች ለእያንዳንዱ ከፍተኛ ባለሙያዎቻቸው እና ሌሎች ሰራተኞቻቸው ባለስልጣኑ በየጊዜው በሚደነግገው ወይም በሚጠይቀው መሠረት በሚመለከተው የመንግስት አካል የተሰጠ ከወንጀሎች ነጻ መሆንን የሚያስረዳ የምስክር ወረቀት ሊኖራቸው ይገባል፤

(3) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ሁለት የተጠቀሰው ከወንጀል ነጻ የመሆን የምስክር ወረቀት ሰራተኞቹ ከመሾማቸው ወይም ከመቀጠራቸው በፊት መቅረብ ይኖርበታል፡፡

(4) ራሱን በራሱ የሚቆጣጠር ድርጅት እና ከፍተኛ ባለሙያዎቹ የብቁና የተገቢነት መስፈርቶችን እንዳሟሉ የሚቆጠረው፡-

ሀ) ራሱን በራሱ የሚቆጣጠረውን ድርጅት ተግባራት ለማከናወን የሚያስፈልገውን ዝቅተኛውን ብቃት፣ ክህሎት እና ልምድ እንዳላቸው ለባለስልጣኑ ሲያረጋግጡ፤

ለ) ከማታለል፣ ስርቆት፣ እምነት ማጉደል ወይም ገበያን ማዛባት እና የፋይናንስ ወንጀል ጋር በተያያዘ በወንጀል ጥፋተኛ ካልተባሉ፤

ሐ) በሚመለከተው አስተዳደራዊ አካል ከገንዘብ ተቋማት ተግባራት ጋር በተያያዘ ጥፋት በመስራት ካልተወሰነባቸው፤

መ) የመክሰር ውሳኔ ያልተሰጠባቸው ከሆኑ፤

ሠ) በኪሳራ ምክንያት ንብረት የማጣራት ሂደት ውስጥ ያልገቡ ከሆኑ፤

ረ) በበቂ ምክንያት ከማንኛውም የሙያ ተቋም፣ ማህበር ወይም አባልነት ተሰርዞ ወይም ተባርረው የማያውቁ ወይም ሙያን የመተግበር ወይም ስራን የማከናወን ፈቃድ ያልተነጠቁ ከሆኑ፤

ሰ) ከማንኛውም የሰነደ ሙዓለንዋይ ገበያ ወይም ካልተማከለ የጠረጴዛ ዙሪያ ገበያ አገልግሎት ያልተወገዱ ከሆኑ፤

ሸ) በአካላዊ ወይም አዕምሯዊ ህመም ምክንያት ችሎታውን ያላጡ ከሆኑ ፡፡

ነው።

18. ዋና የሕግ ማስከበር መኮንን

(1) እያንዳንዱ ራሱን በራሱ የሚቆጣጠር ድርጅት ለባለስልጣኑ አስቀድሞ በማሳወቅ የአዋጁን፣ በባለስልጣኑ የሚወጡ መመሪያዎችን እና ሌሎች አግባብነት ያላቸውን ሕጎች መከበራቸውን የመከታተልና የማረጋገጥ ኃላፊነት ያለበትን ዋና የሕግ ማስከበር መኮንን መሾም አለበት፡፡

(2) ዋና የሕግ ማስከበር መኮንኑ ማንኛውንም የአዋጁን፣ የዚህን መመሪያ፣ ወይም ሌላ ማንኛውም አግባብነት ያለው ሕግ፣ ፖሊሲዎች ወይም ደንቦች ጥሰቶች ወይም ያለመከበር ሲያውቅ ወዲያውኑ ያለማንም ጣልቃ ገብነት ለባለስልጣኑ ማሳወቅ አለበት፡ ፡

(3) ዋና የሕግ ማስከበር መኮንን ለሌሎች ሰራተኞች ከሕግ ማክበር ጋር በተያያዙ ጉዳዮች ላይ ዓመታዊ ስልጠና የማዘጋጀት እና ሌሎች በባለስልጣኑ የሚወሰኑ ተግባራትን የማከናወን ሀላፊነት ይኖርበታል።

(4) እያንዳንዱ ራሱን በራሱ የሚቆጣጠር ድርጅት ዋና የሕግ ማስከበር መኮንኑን ወደ ሌላ ኃላፊነት ከመመደቡ ወይም ከማሰናበቱ በፊት በጽሁፍ ለባለስልጣኑ ማሳወቅ አለበት፡፡

(5) በማንኛውም ሁኔታ ቢሆን የዋና የሕግ ማስከበር መኮንን የስራ መደብ ከአንድ (1) የሥራ ቀን በላይ ክፍት መሆን የለበትም፤

(6) ራሱን በራሱ የሚቆጣጠር ድርጅት የስራ መደቡ ክፍት በሚሆንበት ጊዜ የዋና ሕግ ማስከበር መኮንን ሊሆኑ የሚችሉ የውስጥ ሰራተኞችን ወዲያውኑ በመለየት ለመተካት የሚያስችል ውጤታማ የመተካካት ዕቅድ ሊኖረው ይገባል፡፡

19. ጉልህ ለውጦች

(1) ራሱን በራሱ የሚቆጣጠር ድርጅት በአዋጁ አንቀጽ 24 እና 27 መሰረት ጉልህ ለውጦች ሲኖሩ ለባለስልጣኑ በጽሁፍ ማሳወቅ አለበት፡፡

(2) ባለስልጣኑ ስለየአባላት ስብጥር ለውጥ ማሳወቅያ  በደረሰው በአስራ አምስት (15) ቀናት ውስጥ ተቃውሞውን ያልገለጸ እንደሆነ  የአባላት ስብጥር ለውጥ የጸና ይሆናል፡፡

(3) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) የተገለጸው ቢኖርም በዲሲፕሊን እርምጃ ምክንያት የተፈጠረ የአባላት ስብጥር ለውጥ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 22 መሠረት ይወሰናል፡፡

(4) የከፍተኛ ባለሙያዎች፣ የዋና የሕግ ማስከበር መኮንን ወይም የቦርድ ዳይሬክተር ሹመት ወይም ለውጥ በአዋጁ አንቀጽ 27 ድንጋጌዎች መመራት አለበት፡፡

(5) ራሱን በራሱ የሚቆጣጠር ድርጅት ከፍተኛ ባለሙያዎች ስንብት በአዋጁ አንቀጽ 28 ድንጋጌዎች መመራት አለበት፡፡

(6) ራሱን በራሱ የሚቆጣጠር ድርጅት፡-

(ሀ) የከፍተኛ ባለሙያው ወይም የቦርድ ዳይሬክተሩ ስራ መልቀቅ ተፈጻሚ ከሚሆንበት ቀን አስቀድሞ ከአምስት (5) የስራ ቀናት በላይ ሳይዘገይ ወይም ከፍተኛ ባለሙያው ወይም የቦርድ ዳይሬክተሩ የስራ መልቀቂያ ባስገቡ በአስር (10) ቀናት ከሁለቱ ቀድሞ በሚደርሰው ጊዜ ውስጥ፤ እና
(ለ) የከፍተኛ ባለሙያውን ወይም የቦርድ ዳይሬክተሩን መሞት ባወቀ በአምስት (5) ቀናት ውስጥ

ለባለስልጣኑ ማሳወቅ አለበት፡፡

20. ራሱን በራሱ የሚቆጣጠር ድርጅት ቢሮ

(1) እያንዳንዱ ራሱን በራሱ የሚቆጣጠር ድርጅት: -

ሀ) ዋና መስሪያ ቤቱን ከመቀየሩ፤

ለ) አዲስ ቅርንጫፍ ከመክፈቱ፤ እና

ሐ) የትኛውንም ቅርንጫፉን ከመዝጋቱ ወይም አድራሻውን ከመቀየሩ፤

በፊት አስቀድሞ ለባለስልጣኑ በጽሁፍ ማሳወቅ አለበት፡፡

(2) የቢሮ አድራሻ ለውጥ ወይም መዝጋት ተፈጻሚ የሚሆነው፡-

ሀ) ባለስልጣኑ መረጃው በደረሰው በአስራ አምስት (15) ቀናት ውስጥ ተቃውሞውን ካልገለጸ፤ እና

ለ) ራሱን በራሱ ለሚቆጣጠረው ድርጅት አባላትና ለጠቅላላው ሕዝብ ቢሮውን የመዝጋቱን ወይም አድርሻውን የመቀየሩን ሀሳብ ቢያንስ ከአስራ አምስት (15) ቀናት በፊት እንዲያውቁት ከተደረገ ነው፡፡ መረጃው የሚሰጠው በአባላቱ የኢሜይል አድራሻ ፣ ራሱን በራሱ በሚቆጣጠረው ድርጅት ድረ-ገጽ ላይ በማውጣት እና

ሁለት (2) ሰፊ ስርጭት ባላቸው የእንግሊዘኛ እና አማርኛ ቋንቋዎች የዲጂታል ወይም የወረቀት ጋዜጦች ላይ በማሳተም ነው፡፡

21. ሪከርዶችን ስለመጠበቅ

(1) ራሱን በራሱ የሚቆጣጠር ድርጅት፡-

ሀ) ግብይቶችን እና የድርጅቱን ሀብቶች የባለቤትነት ዝውውር የሚያሳዩና በኢትዮጵያ የሂሳብ አያያዝና ኦዲት ቦርድ በወጡ የሂሳብ አያያዝ መመሪያዎች መሠረት የተዘጋጁ መዛግብትን፣ ሪኮርዶችንና ትክክለኛ ዝርዝር ሂሳቦችን መያዝና ማስቀመጥ አለበት፤

ለ) ስለ አባላቱ ተገቢውን የተሟላ፣ ትክክለኛ፣ እና ደህንነቱ የተረጋገጠ ሪከርድ ማስቀመጥ አለበት፤ እና

ሐ) ለባለስልጣኑ መዛግብቱ፣ ሂሳቦቹና ሰነዶቹ ስለተቀመጡበት ቦታ እና ሁኔታ መረጃ መስጠት አለበት፡፡

(2) የአባላት ሪከርዶች የሕትመት፣ የኤሌትሮኒክ እና የድምጽ ቅጂዎችን ባጣመረ ሁኔታ ሊቀመጡ ይችላሉ፡፡

(3) ራሳቸውን በራሳቸው የሚቆጣጠሩ ድርጅቶች የአባላት ሪኮርዶች እንዳይጠፉ ወይም እንዳይበላሹ አስፈላጊ የሆኑ ጥንቃቄዎችን ማድረግና የሪኮርዶችን በቂ ምትክ ከዋና የስራ ቦታቸው ውጭ ማስቀመጥ አለባቸው፡፡

(4) ራሱን በራሱ የሚቆጣጠር ድርጅት ሁሉንም ሪከርዶቹን፣ ካዘጋጃቸው ወይም ከተቀበላቸው ቀን ጀምሮ ለአስር (10) ዓመታት መያዝና ማቆየት አለበት፤ በዚህ ቆይታ ጊዜ ሪኮርዶቹ ለባለስልጣኑ ምርመራ ክፍት መሆን አለባቸው፡፡

22. ሪፖርት የማድረግ ግዴታ

(1) ራሱን በራሱ የሚቆጣጠር ድርጅት፣ ከፍተኛ ባለሙያው ወይም ሌሎች ሰራተኞቹ ማንኛውንም፡-

ሀ) የአዋጁን፣ የዚህን መመሪያ ጥሰት ጥሰቱ መፈጸሙን ባወቀ በሃያ አራት (24) ሰዓት ውስጥ እና ሊወሰድ የታሰበውን እርምጃ፣ እና

ለ) የተከለከሉ የግብይት ተግባራት መፈጸማቸውን ሲጠረጥር ድርጊቱ መፈጸሙን ወይም ጥርጣሬ መኖሩን ባወቀ በሃያ አራት (24) ሰዓት ውስጥ

ለባለስልጣኑ ሪፖርት ማድረግ አለባቸው፡፡

(2) እያንዳንዱ ራሱን በራሱ የሚቆጣጠር ድርጅት በባለስልጣኑ የሚወሰን ቅጾችን ተከትሎ፣

ሀ) የሩብ ዓመቱ ባለቀ በሰላሳ (30) ቀናት ውስጥ የቅኝትና የምርመራ ስራዎቹን ፣ የክትትል ስራዎችን፣ በአባላት ላይ የተወሰዱ የዲሲፕሊን እርምጃዎችን፣ እና የአለመግባባት አፈታትን ስራዎቹን በተመለከተ የሩብ ዓመት ሪፖርት፣

ለ) በአዋጁ አንቀጽ 29 መሰረት ዓመታዊ ሪፖርት፣ እና

ሐ) በአዋጁ ወይም በዚህ መመሪያ በተቀመጠው አግባብ ራሱን በራሱ ከሚቆጣጠር ድርጅት ሀላፊነት ጋር በተገናኘ ሌላ ማንኛውም ባለስልጣኑ የሚጠይቀው መረጃ፣

ማቅረብ አለበት፡፡

23. ስርዓቶች እና ቁጥጥሮች

(1) ራሱን በራሱ የሚቆጣጠር ድርጅትአግባብነት ያላቸውን ሕግና ደንብ ጥሰቶችን ለመከላከል፣ ለመለየት እና የማስተካከያ እርምጃ ለመውሰድ የሚያስችል ተገቢና በቂ የውስጥ ቁጥጥር አሰራር ፣የአደጋ ስጋት አስተዳደር ስርዓቶች እና የሕግ ማስከበር ስርዓት ሊኖረው ይገባል፡፡

(2) ስራዎቹንና ተግባሮቹን የቴክኖሎጂ መሳሪያን፣ ስርዓትን ወይም መተግበሪያን በመጠቀም የሚያከናውን ራሱን በራሱ የሚቆጣጠር ድርጅት፡-

ሀ) የቴክኖሎጂ መሳያዎቹ፣ ስርዓቶቹ ወይም መተግበሪያዎቹ ሲበለጽጉ ወይም በተግባር ላይ ሲውሉ የግል መረጃ ጥበቃ ህግጋትና መስፈርቶች ከግምት መግባታቸውንና መከበራቸውን፤

ለ) የዲጂታል አገልግሎቱ ለተጠቃሚ ቀላልና ምቹ የሆኑ መገናኛ ገጽ ያላቸው መሆኑን፣ እና

ሐ) የተጋላጭነትና የመጠቃት መጠን ፍተሻ በየመንፈቁ የሚደረግለት መሆኑን

ማረጋገጥ አለበት፡፡

24. በባለስልጣኑ የሚደረግ ክትትል እና ምርመራ

(1) ባለስልጣኑ በቅድሚያ አሳውቆም ሆነ ሳያሳውቅ ሁሉንም አስፈላጊ መዛግብቶች፣ መረጃዎችና ሪከርዶች ያለገደብ በመመልከት ራሱን በራሱ የሚቆጣጠር ድርጅት የስራ ቦታ ላይ በመገኘት ወይም በርቀት መደበኛና ልዩ ምርመራ ያደርጋል፡፡

(2) ክርቀት ለመከታተል ወይም በስራ ቦታው ላይ በመገኘት ምርመራ ለማድረግ ባለስልጣኑ ከራሱ ሰራተኞች በተጨማሪ እንዳስፈላጊነቱ ኦዲተሮችን፣ ሕግ አስከባሪዎችን እና ሌሎች የህግ አካላትን ሊጠቀም ይችላል፡፡



የኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ ባለስልጣን ETHIOPIAN CAPITAL MARKET AUTHORITY

25. ከምርመራ ወይም ከክትትል ጋር በተያያዘ የሚደረግ ትብብር

(1) ራሳቸውን በራሳቸው የሚቆጣጠሩ ድርጅቶችና ሰራተኞቻቸው በባለስልጣኑ ከሚደረጉ ሁሉም ምርመራዎች ወይም ክትትሎች ጋር የተሟላ ትብብር ማድረግና በባለስልጣኑ ለሚቀርብ የመረጃ ጥያቄ በፍጥነት ምላሽ መስጠት አለባቸው፡፡

(2) ባለስልጣኑ ለምርመራው ወይም ለክትትሉ ዓላማ የሚፈልገውን ማንኛውንም መረጃ የመጠየቅ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡

26. የደንበኞች ካሣ ፈንድ

(1) ራሱን በራሱ የሚቆጣጠር ድርጅት በባለስልጣኑ ፈቃድ የደንበኞች የካሣ ፈንድ ሊያቋቁም ይችላል፡፡

(2) የደንበኞች ካሣ ፈንድ የሚያቋቁም ራሱን በራሱ የሚቆጣጠር ድርጅት ፈንዱ ሁልጊዜም በቂ ገንዘብ ያለው መሆኑን ማረጋገጥ አለበት፡፡

(3) የደንበኞች የካሣ ፈንዱ በባለስልጣኑ የጸደቀ እና ለህዝብ ግልጽ የሆነ የገንዘብ አሰባሰብና አጠቃቀም የአሰራር ስርዐት ሊኖረው ይገባል።

(4) የደንበኞች የካሣ ፈንድ የተጎጂዎችን ጉዳት ለመካስ የሚውለው ራሱን በራሱ የሚቆጣጠረው ድርጅት አግባብነት ባላቸው የካሳ ፈንዱ የአሰራር ስርዐቶች መሰረት የካሳ ጥያቄው ተገቢነት ያለው ነው ብሎ ሲወስን ነው።

(5) የደንበኞች የካሳ ፈንድን በተመለከተ ራሱን በራሱ የሚቆጣጠረው ድርጅት የሚሰጠው የመጨረሻ ውሳኔ ለባለስልጣኑ ይግባኝ ሊጠየቅበት ይችላል።

## ክፍል አራት

## አስተዳደራዊ እርምጃዎች

27. ቅጣቶች እና ሌሎች

(1) በአዋጁ አንቀጽ 107 መሰረት ባለስልጣኑ ራሱን በራሱ የሚቆጣጠር ድርጅት፣ የቦርድ ዳይሬክተሮቹ፣ ከፍተኛ ባለሙያዎቹ እና ሌሎች ሰራተኞቹ ለሚፈጽሙት ጥፋት ከሚከተሉት ቅጣቶች አንዱን ወይም ከአንድ በላይ በማጣመር ሊወስን ይቻላል፡፡

ሀ) የገንዘብ ቅጣት፤

ለ) ለህዝብ ይፋ የሆነ ወይም በግል ማስጠንቀቂያ ወይም ተግሳጽ መስጠት፤

ሐ) በይፋ ወይም በግል ወቀሳ መስጠት፣

መ) ራሱን በራሱ ለሚቆጣጠር ድርጅት የሰጠውን እውቅና መሰረዝ፣

ሠ) ጥፋቱ የሚመለከታቸውን የቦርድ ዳይሬክተሮች፣ ከፍተኛ ባለሙያዎች እና ሰራተኞች ማንሳት፣

ረ) ከፍተኛ ባለሙያዎችን ወይም ሌሎች ሰራተኞችን ተገቢነት የሌላቸው ሰዎች ዝርዝር ውስጥ ማስገባት፣

ሰ) በባለስልጣኑ ለሚወሰን ጊዜ ራሱን በራሱ የሚቆጣጠረውን ድርጅት መመስረቻና መተዳደሪያ ደንብ ድንጋጌ ወይም ውስጠ-ደንብ ማገድ፣

ሸ) ራሱን በራሱ የሚቆጣጠር ድርጅት ውስጠ-ደንቦቹን እንዲቀይር ማስገደድ፣

ቀ) ራሱን በራሱ የሚቆጣጠር ድርጅት መመስረቻ ጽሁፉን፣ መተዳደሪያ ደንቡንና ውስጠ-ደንቦቹን ተግባራዊ እንዲያደርግ ማስገደድ፣ እና

በ. አስተዳደራዊ ክፍያ እንዲከፈሉ ማድረግ

(2) ባለስልጣኑ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ማንኛውንም እርምጃ ከመውሰዱ በፊት ራሱን በራሱ ለሚቆጣጠረው ድርጅት፣ ለአባሎቹ፣ ለቦርድ ዳይሬክተሮቹ ወይም ለከፍተኛ ባለሙያዎቹ እንደ አግባብነቱ የመሰማት መብት መስጠት አለበት፡፡

28. እውቅናን ማንሳት

(1) ባለስልጣኑ በሚከተሉት ምክንያቶች ራሱን በራሱ ለሚቆጣጣር ድርጅት የሰጠውን እውቅና ሊሰርዝ ይችላል።

ሀ) ራሱን በራሱ የሚቆጣጠረው ድርጅት በዚህ መመሪያ አንቀጽ 8 መሰረት እውቅና የማግኘቱ ማስታወቂያ ከታተመ በኋላ በአንድ (1) ዓመት ውስጥ ስራ ካልጀመረ፣

ለ) ራሱን በራሱ የሚቆጣጠረው ድርጅት አዋጁንና አዋጁን ተከትለው የወጡ ህጎችን እና በውስጠ-ደንቦቹ መሰረት ስራዎቹን በአግባቡ አለማከናወኑ ወይም ግዴታዎቹንና ተግባራቱን ለመፈጸም የማይችል ስለመሆኑ ባለስልጣኑ ሲወስን፣

ሐ. ባለስልጣኑ፡-

i. ራሱን በራሱ የሚቆጣጠረው ድርጅት ማንኛውንም የአዋጁን ወይም የዚህን መመሪያ ድንጋጌ ያላከበረ መሆኑን ካረጋገጠ ፣
ii. ራሱን በራሱ የሚቆጣጠረው ድርጅት መክሰሩ ከታወጀ፣ወይም

iii. ራሱን በራሱ የሚቆጣጠረው ድርጅት ስራውን ማከናወን ካቆመ፣

መ. ራሱን በራሱ የሚቆጣጠረው ድርጅት በራሱ ፈቃድ ስራ ለማቆም መወሰኑን ለባለስልጣኑ በማመልከቻ ካሳወቀ፣

(2) ባለስልጣኑ ራሱን በራሱ የሚቆጣጠር ድርጅትን እውቅና ለመሰረዝ ያስተላለፈው ውሳኔ በኢትዮጵያ ውስጥ ሰፊ ስርጭት ባለው ጋዜጣ መታተም አለበት፡፡

29. ይግባኝ የመጠየቅ ስነ-ስርዓት

ራሱን በራሱ የሚቆጣጠር ድርጅት በባለስልጣኑ ውሳኔ ቅሬታ ያለው እንደሆነ በአዋጁ ክፍል ሰባት በተደነገገው መሠረት ለካፒታል ገበያ አስተዳደር ፍርድ ቤት ይግባኝ ለማለት ይችላል፡፡

## ክፍል አምስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

30. ተፈጻሚነት የማይኖራቸው ሕጎች

ይህን መመሪያ የሚቃረን ሌላ ማንኛውም መመሪያ ወይም ልማዳዊ አሰራር በዚህ መመሪያ በተመለከቱት ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚ አይሆንም፡፡

31. መመሪያው የሚጸናበት ቀን

ይህ መመሪያ በፍትሕ ሚኒስቴር ተመዝግቦ በባለስልጣኑ ይፋዊ ድረ-ገጽ ላይ ከተጫነበት ቀን ጀምሮ ተፈጻሚ ይሆናል።

አዲስ አበባ ፡ ሕዳር 2017 ዓ.ም

ሀና ተኸልቁ

የኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ ባለስልጣን

ዋና ዳይሬክተር